**የእጩው ስም፦** Brendan Kolding
**የዘመቻ ስም፦** Kolding ለ ዲስትሪክት 1
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፦** www.BrendanKolding.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፦** 1
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** (206) 458-4408
**የእጩ ማስተዋወቂያ፦**

ሲያትል ስልጡን ከተማ ናት። ዓለም-ቀያሪ ሃስቦች ከዚች መንጭተዋል። እነዚህ ሃሳቦች እድገትንና አዳጊ ችግሮችን አስከትለዋል። በከተማ ምክር ቤት ያለው የፓርቲ ጽንፍ የያዘ ፖለቲካ ለእነዚህ አዳጊ ችግሮች የታሳቡ ምላሾችን ከልክሏል። ለከተማው ሀብቶች መልካም አስተዳዳሪ ከመሆን ፋንታ፣ የከተማው ምክር ቤት ግብሮችን በማሳደግ በማተኮር አነስተኛ ንግዶች እና ቤተሰቦች ኑሮን ለመቋቋም አስቸጋሪ አድርግባቸዋል። በሺዎች የሚቆጠሩ በረንዳ አዳሪ ናቸው። ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ሰዎች በጎዳናዎች ይዘዋወራሉ። የፖሊስ መምሪያው እየቀጨጨ መጥቷል። የተሽከርካሪ ፍሰቱም አስደንጋጭ ነው። ስልጡኗ ከተማ ቀውስ ላይ ነች።

የማህበራዊ አገልግሎቶች በብዛት የተከማቹበት የአስቸኳይ ጊዜ የመኖሪያ ቤት ክልላዊ መረብ መፍጠር እፈልጋለሁ። የእኛ የፖሊስ መኮነኖች ስራቸውን እንዲያከናውኑ ክብር የሚሰማቸው እና አቅም ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ እፈልጋለሁ። የታሰበበት የእድገት ልማዶችን እፈልጋለሁ። በቂ የህዝብ መጓጓዣ እፈለጋለሁ። ኃላፊነት የተሞላበት የህዝብ ገንዘብ አያያዝ እና ግልጽ አወጣጥ እፈልጋለሁ። የተሞከሮ እውቀት እና ብልህ ውይይቶችን ወደ ከተማው አስተዳደር ማምጣት እፈልጋለሁ። ወደ ሲያትልስልጡን መንግስት ማምጣት እፈልጋለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፦** Lisa Herbold
**የዘመቻ ስም:** District 1 for Herbold
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** district1forherbold.org
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር:** 1
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር:** የለም
**የእጩ ማስታወቂያ:**

ስራ የጀመርኩት በ1998 በመንግስት ስራ ነው፤ ከ2015 ጀምሮ በከተማ አስተዳደር ውስጥ አገልግያለሁ፡፡ የ Seattleን እየሰፋ የመጣ የገቢ ልዩነት ለመፍታት ከ Alki እስከ South Park እና በመካከል የሚገኙ አካባቢዎች ጠንካራ፣ ምላሽ ሰጪ እና ውጤታማ የከልል አገልግሎቶች ፖሊሲዎች ሰጥቻለሁ፡፡
አውራጃ 1 የከተማ አስተዳደር አባል እንደመሆኔ መጠን በሌሎች ከተማዎች እየተቀረጹ ያሉ ናሙና ፖሊሲዎችን ለማስቀረጽ እገዛ አድርጌያለሁ፦ ክፍያ ያለው የህመም ጊዜ እረፈት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ምደባ፣ የኪራይ ምርመራ መርሀግብር፣ የገቢ ምንጭ ልዩነት ከልከላ፣ የ$29 ሚልየን ተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ቦንድ፣ ወንጀል ፍትህ ቅየሳ መርሀግብር እና ሰዎች ቤት፣ የመንግስት ጥቅማ-ጥቅም ወይም ፈቃዶችን እንዳያጡ የህግ ድጋፍ መርሀግብር፡፡

ከከተማ መስተዳደር በፊት ማህበረሰቤን በተለያየ የስራ ደረጃ አገልግለያለሁ፤ የጎዳና ተዳዳሪዎች መጠለያ፣ የተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ድርጅት፣ አነስተኛ ገቢ አካባቢ ድርጅት እና የአከራይ ድርጅትን ጨምሮ፡፡

ሴት ልጅ፣ ሴት የልጅ-ልጅ እና ወንድ የልጅ-ልጅ አለኝ፡፡ ለባበለቤቴ ሁለት ሴት ልጆች እንጀራ እናት ነኝ፡፡ Highland Park የኖርኩት ከ2000 ጀምሮ ነው፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** ፊል ታቬል [Phil Tavel]
**የዘመቻ ስም፡-** ታቬል ለ ሲያትል [Tavel for Seattle]
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** tavelforseattle.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 1
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-949-8680
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ሲያትል መስቀለኛ መንገድ ላይ ነች። ስር የሰደዱ የህዝብ ደህንነት ጉዳዮች መጨመራቸውን ቀጥለዋል። ይፋ የአደገኛ እጽ ስርጭት እና አጠቃቀም የተለመዱ ሆነዋል። እንደ አንድ ጠበቃ ሆኘ ያገለገልኩበት አመታት ለወንጀል ፍትህ ስርዓት እይታዎችን አበርክቷል፣ እኔ እንደማምነው የአእምሮ ጤና ችግሮች እና/ወይም ንጥረ ነገርን ያላግባብ የመጠቀም ቀውስ ላጋጠማቸው ሰዎች ለመርዳት የበለጠ ማድረግ ይችላል። ሲያትል የተሻለ ማድረግ ትችላለች።

የቤት የለሽነትን ቀውስ ለመፍታት ከተማዋ የምታደርገው ጥረት መጠለያ የሌለው ህዝብ ከመጨመሩ ፍጥነት ጋር አብሮ መራመድ አልቻለም።

የመካከለኛ መደብ ነዋሪዎች በውድነት ከተማዋን ለቀዋል፣ የመኪና ፍሰቱ ከፍቷል እና የእኛ ተመራጭ ባለስልጣናት ባሉበት የደረቁ ይመስላሉ። በ D1 ውስጥ እና በመላው ከተማ ያሉ ማህረሰቦች እና የአካባቢው የንግድ ባለቤቶች እንደተተው እና የሚሰማቸው እንደሌለ ይሰማቸዋል።

የ ሲያትል ልማድ'Seattle Way' እንደ አንድ መጨረሻ እንደሌለው የረባ ውጤት የማያስገኝ ጥልፍልፍ ሂደቶች መሆኑ በሰፊው ይታወቃል። አንድ ችግሮችን የሚፈታ እና መፍትሄዎች ላይ የሚያተኩር አዲስ የሲያትል ልማድ'Seattle Way' ጊዜ ነው።

የለውጥ ጊዜ ነው። እባክዎ የዲስትሪክት 1 [District] ፊል ታቬል [Phil Tavel] ይምረጡ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Ari Hoffman
**የዘመቻ ስም:** Hoffman for Seattle
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** www.hoffmanforseattle.com
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 2
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-775-8767
**የእጩ ማስታወቂያ:**

Ari Hoffman የሚወዳደሩት ለከተማ አስተዳደር፣ አውራጃ 2 ነው፤ የሚወዳደሩትም የቤት አልባ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ Ariን የበለጠ ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ Seattle ለመፍጠር ስላነሳሳቸው ነው:: Seattle ለተለመደ፣ ስሜትን ያገናዘበ እና ተግባራዊ መፍትሄዎች ዝግጁ ነው:: Ari የሚያገለግሉት እጽ አዘዋዋሪዎች እና ሴተኛ አዳሪዎች የግል ቤቶች ሰብረው በገቡበት፣ መቃብር ድንጋዮችን በሰባበሩበት እና ጠባቂዎቹን ባጠቁበት በ Jewish የመቃብር ቦታ ወሰን ላይ ነው:: Ari የመገናኛ ብዙሀን ግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ ጀምረዋል፣ ከከተማ አስተዳደር አባላት፣ ማህበረሰብ አባላት እና የፖሊስ መምሪያው ጋር ተገናኝተዋል:: በዚህ ሂደትም የበጀት ጉዳዮች፣ ቢሮክራሲ እና በስርዐቱ ውስጥ ያሉ ሂደቶች ተጋልጠዋል:: Ari የሄድ ግብርን ይቃወማሉ፤ ስር ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር በመሆን ሪፈረንደሙን ለማሻር በቂ ፊርማ አሰባስበዋል:: Ari የሚኖሩት እና የሚሰሩት ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት እና ከመላው Seattle ሰዎች በሚቀጥሩበት አውራጃ 2 ውስጥ ነው:: በበጎ ፈቃድ ስራ የወጣቶች መርሀግብሮችን በማካሄድ በርካታ አመታትን አሳልፈዋል:: Ari በርካታ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ቦርድ ውስጥ ያገለግላሉ እንዲሁም የት/ቤቶች እና ማህበረሰብ መሰረተ-ልማቶችን ለመገንባት እገዛ አድርገዋል::

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር ላይ አይሳተፉም::*

**የእጩው ስም፡-** Christopher Peguero
**የዘመቻ ስም:** District 2 for Peguero
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** christopher@district2forpeguero.com
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 2
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-665-4338
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

Christopher Peguero አባት፣ ባል እና አዝናኝ የላቲን እና አሜሪካ ተወላጅ ሲሆን ለአየር ንብረት፣ ዘር እና የማህበራዊ ፍትህ ይከራከራሉ፡፡ እሳቸው እና ባለቤታቸው Anthony ከልጆቻው Alexander እና Adela ጋር በ Beacon Hill ይኖራሉ፡፡

Christopher በ Seattle የከተማ መብራት ከአስርተ አመታት በላይ ሰርተዋል፤ የከተማውን የዘር እና የማህበራዊ ፍትህ ቅስቀሳ መሳሪያ ለእኩልነት እና ፍትህ መከራከሪያነት ተጠቅመዋል፡፡ የ Seattle የተመሳሳይ ነገሮች እኩልነት ቡድን መስራች ናቸው፤ ከወሲባዊ ዝንባሌ ወይም ጾታዊ ማንነት ባሻገር በስራ ቦታ ላይ መኖር ስላለበት ፍትህ ይከራከራሉ፡፡ የእሳቸው ተቀዳሚ ግብ ግለጽነት፣ ፍትህ እና የመንግስት የባህል ተደራሽነትን ከማህበረሰብ ጋር መስራት ነው፡፡

Christopher የ Seattle ከተማ አስተዳደር አውራጃ 2 እጩ ናቸው፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** Mark Solomon
**የዘመቻ ስም:** Friends for Mark Solomon
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** marksolomon.org
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 2
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-679-1162
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

ስሜ Mark Solomon ነው፤ የ Seattle ከተማ አስተዳደር፣ አውራጃ 2 እጩ ነኝ፡፡ ተወልጄ ያደኩት አውራጃ 2 ውስጥ ነው፤ አያቴ የሰራችው ቤት ውስጥ በመኖሬ እድለኛ ነኝ፡፡ ይህ የኔ ማህበረሰብ ሲሆን ሰዉም ጎረቤቴ ነው፤ ለውጦቹን አይቻቸዋለሁ እንዲሁም ስጋቶቹ ገባኛል፡፡ ለ30 አመታት አካባቢ አካባቢያችን ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩ የህዝብ ደህንነት እና የህይወት ጥራት ጉዳዮች ላይ ሰርቻለሁ፡፡ መልካም ውጤት ለማምጣት ሰዎችን የማሰባሰብ ታሪክ አለኝ፡፡ ለረዥም ጊዜ የከተማ አስተዳደር የዚህን አውራጃ ፍልጎቶች እና ስጋቶች አዘግይቷል፤ ስለዚህ ማንኛውም ጉዳይ ከተማ አስተዳደሩ ጋር ሲቀርብ የመጀመሪያ ሀሳቤ ጉዳዩ እንዴት አውራጃው ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ነው፡፡ ለአውራጃው ነዋሪ ምላሽ ሰጪ፣ ተደራሽ እና ተጠያቂ ለመሆን ቃል እገባለሁ፡፡ ድጋፋችሁን፣ ምርጫችሁን እና በይበልጥ አመኔታችሁን እጠይቃለሁ፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** ፊሊስ ፖርተር [Phyllis Porter]
**የዘመቻ ስም፡-** ሰዎች ለ ፊሊስ ፖርተር [Phyllis Porter]
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** electphyllisporter.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 2
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-582-5150
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ዲስትሪክት 2 [District የተለያየ መነሻዎች እና ማህበረኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያላቸው ቤተሰቦች የሚኖሩባት እና የሚጥሩባት ቦታ መሆኗን ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ሰዎች በቤታቸው ውስጥ እንዲቆዩ ማድረግ እና በይበልጥ ለሚያስፈልጋቸው መኖሪያ ቤት እንዲያገኙ መርዳት አለብን። በመፈናቀል ተጋልጭ የሆኑትን፣ እንዲሁም የሚከተሉትን አካቶ የሚደግፉ ፖሊሲዎችን ለማስፋፋት እሰራለሁ፦ የለቀው ይውጡ ጥበቃዎች፣ የብድር ማማከር፣ መጓጓዣ እና የውሃ ፣ መብራት እና ጋዝ እገዛ፣ የህግ እና የስራ ድጋፍ አገልግሎቶች፣ እና የአጭር ጊዜ የክራይ ድጋፍ።

በ ዲስትሪክት 2 [District ውስጥ በርካታ ነዋሪዎች ለዕለታዊ ጉዞ የህዝብ መጓጓዣን፣ ብስክሌተ ወይም የእግር ጉዞ ላይ ይመካሉ። የእኛ ዲስትሪክት በከተማ ውስጥ የሚገኙ እግረኞችን እና ብስክሌተኞችን ያካተተ እጅግ ከፍተኛ መጠን ጉዳቶች ይደርሳሉ፣ እና እኔ ይህን ችግር ለመፍታት እራሴን ሰጥቻለሁ።

እንድ አንድ ልምድ እንዳለው አደራጅ እና ለደቡብ ሲያትል [South Seattle] ደህንነት ተሟጋች፣ በቂ ውክልና የሌላቸውን ማህረሰቦችን ወደ ጠረጴዛው ማምጣቴን እቀጥላለሁ። ሁሉም ሰው ሊደመጥ ይገባዋል፣ እና እኔ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል ለማዳመጥ እና ለእናንተ ለመሟገት እሰራለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Tammy Morales
**የዘመቻ ስም:** People for Tammy Morales
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** www.votefortammy.com
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 2
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206.399.0478
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

የምወዳደረው በአውራጃ 2 ለሚገኙ ጎረቤቶቻችን ሀይል ለመገንባት ነው፡፡ ሀሳባችሁን በመስማት እና በከተማ ፖሊሲ ከፍተኛ ተጽዕኖ የደረሰባቸው ማለትም አነስተኛ ገቢ ያላቸው የሚሰሩ ጎረቤቶቻችን፣ አረጋውያን፣ ስደተኞች፣ አካል ጉዳተኛ ጎረቤቶች እና ከነጭ ሌላ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦችን በማስቀደም አምናለሁ፡፡
የብቸኛ እናት ልጅ እንደመሆኔ መጠን የሚሰሩ ቤተሰቦች ሁኔታዎችን ለማሟላት የሚያሳልፉትን ችግር በቅርበት አይቻለሁ፡፡

ከ ሬነር ባህር ዳርቻ የትግበራ ህብረት (Rainier Beach Action Coalition) ጋር አዘጋጅ የሆንኩት ለሚሰሩ ቤተሰቦች ለመዋጋት ነው፡፡ የ Seattle ሰብአዊ መብት ኮሚቴ ኢጋር ሊቀመንበር የሆንኩትም ለዚሁ ነው፡፡ በዚህ ሩጫ ላይ የኮንግረስ አባል Jayapal ሲመሰክሩልኝ የሚሰሩ ቤተሰቦች ጀግና ብለው የጠሩኝም ለዚሁ ነው፡፡

ከተማው ለሁላችንም የሚሰራበት ሰአት ነው፤ ለተወሰኑት ሀብታሞች ብቻ ሳይሆን፡፡ ከተመረጥኩ እናንተን መስማት እንደምቀጥል እና ድምጻችሁን ወደከተማ አስተዳደሩ እንደማቀርብ ቃል እገባለሁ፡፡

ድምጻችሁን እና ቮውቸር እንድትሰጡኝ እጠይቃለሁ፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** አሚ ኒግዮን\
**የዘመቻ ስም፡-** የአሚ ኒግዮን\ ጓደኞች
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.electami.com
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 3
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-225-4671
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
የቪዬትናምዊ ስደተኞች ልጅ ነኝ እናም ያደኩትም በድህነት ነው። በመንግሥት የእገዛ መርሐግብርች እና በህዝባዊ ትምህርት እገዛ፣ ከስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ\ ለመመረቅ ችያለሁ። የህግ ሙያዬን ለሕዝብ አገልግሎት ሰጥቻለሁ። እንደ አንድ የህዝብ ተሟጋች፣ ከቤት እጦት፣ የአእምሮ ህመም እና ሱሰኝነትን እየታገሉ ካሉ ሰዎች ጋር እሰራለሁ።

የቤት የለሽነት ችግርን እና የመከፈል አቅምን ጉዳዮች ለመፍታት የላቀ ልምድ እና ክህሎት አለኝ። በአስቸኳይ መኖሪያ ቤት መገንባት፣ ድጋፍ ሰጭ ቋሚ መኖሪያ ቤት እና የሁለተኛ እድል የሥራ መርሐግብሮች ላይ የሚያተኩር የአምስት ዓመት ዕቅድ መስራት ያስፈልገናል። ሰዎች በመኖሪያ ውስጥ እንዲቆዩ እና ቋሚ ገቢ ላላቸዉ አዛውንቶች በክፍለ-ግዛት ገቢ ላይ የተመሰረተ የንብረት ግብር ጭማሪ ነጻ ማድረግ አለብን። ተመጣጣኝ ዋጋ የቤት ማለት ለመኖሪያ ቤት ወጪን ዝቅ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን መጓጓዣ፣ የህጻናት እንክብካቤ እና የምግብ ወጪዎች ይጨምራል። የአረንጓዴው ሃይል ጥረታችን ለሁሉም አይነት ገቢ ላላቸው ሰዎች ተደራሽ መሆን አለበት። በጋራ በመሆን፣ ሲያትል ለሁላችንም የምትሆን ቦታ ማድረግ እንችላለን።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ኢጋን ኦሪዮን\
**የዘመቻ ስም፡-** ኢጋን\ ለ ሲያትል
**የዘመቻ ድረ ገጽ፡-** EganForSeattle.org
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 3
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-682-7328
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
እንደ አራተኛ ትውልድ የዲስትሪክ 3 ነዋሪ፣ ሲያትል ስትለወጥ፣ ስታድግ እና ስትበልጽግ አይቻለሁ። ነገር ግን ከጎረቤቶቼ ብዙዎቹ ሲዘነጉ ተመልክቻለሁ፣ የከተማው ምክር ቤት እየናሩ ያሉትን የቤት ወጪዎችን፣ የሱስ ወረርሽኝን፣ እና የቤት የልሽነት ቀውስን በትክክል ምላሽ ሳይሰጥ ቀርተዋል። የምንገጥማቸው ችግሮች አስጨናቂዎች ናቸው፣ ነገር ግን እኛ ሲያትሎች አዳዲስ መፍትሄዎችን ፈጣሪዎች ነን። አዲስ የትብብር አመራር ድልድዮችን ከሚገነቡ እንጂ ከማያቃጥሉ የምክር ቤት አባላት ጋር ያስፈልገናል።

የምክር ቤት አባል ሳወንት ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሳትሰጥ ስትቀር፣ እሷን አልፌ ነበር የመኖሪያ ቤት የለሽ ተደራሽ ሰራተኞችን ወደ ጎረቤታችን ለመመለስ የሄድኩት። የLGBTQ ማህበረሰብ የክብር ዝግጅት በባለቤትነት የሚወስድ ሰው ስፈልግ፣ እኔም እርምጃ በመውሰድ በሲያትል ውስጥ ትልቁ በዓል እንዲሆን አሳድጌዋለሁ። የብሮድዌይ ጥንካሬ ዳግም እንዲመለስ ረድቻለሁ። ሥራዬን እንደ ለትርፍ ላልተቋቋመ፣ አነስተኛ ንግድ፣ LGBTQ መሪ የማህበረሰብ ግንባታ እና ችግሮችን በመፍታት አሳልፌያለሁ። ከተመረጥኩ፣ ለሲያትል አዲስ ጅምር ለመፍጠር ከእርስዎ ጋር አብሬ እሰራለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ክሻማ ሳዋንት [Kshama Sawant]
**የዘመቻ ስም፡-** ሳዋንት[Sawant 2019] ምረጡ
**የዘመቻ ድረ ገጽ፡-** KshamaSawant.org
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 3
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-486-0099
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

በዚህ ዓመት ትልቁ ጉዳይ ምንድን ነው ሲያትልን ማን እያንቀሳቀሳት ነው — አማዞን [Amazon] እና ትላልቅ የንግድ ድርጅቶች ወይስ ሰራተኛው
ህዝብ። በእኔ በሁለት ምርጫ ጊዜወቼ የስራ ድርሻየን ንቅናቄዎችን ለመገንባት
$15/ሰዓት ዝቅተኛ ምንዳ ክፍያ፣ የተከራይ መብቶች ልክ ለቆ የመግቢያ የክፍያ ጣራ የመሰሉ ታሪካዊ ድሎችን ለማሸነፍ
እና የክፍያ እቅድ፣ እና የኮሎምበስ ቀን “Columbus Day” በ አገር በቀል የህዝቦች ቀን [Indigenous Peoples’ Day] ለመቀየር ተጠቅሜበታለሁ።

ሲያትል ባስቸኳይ የከራይ ቁጥጥር ያስፈልጋታል እና ማህበራዊ የመኖሪያ ቤት ከፍተኛ ማስፋፊያ ግንባታ
(ከፍተኛ-ጥራት፣ በህዝብ ባለቤትነት የተያዘ፣ በዘላቂነት-ተመጣጣኝ ክፍያ መኖሪያ ቤት) በ አማዞን
እና ትላልቅ የንግድ ድርጅቶች በተጣለ ግብር ገንዘብ የተደገፈ፣ በሰራተኛ ቤተሰቦች ወይም አነስተኛ የንግድ ስራዎች ያልሆነ።
አዲስ አረንጓዴ ስምምነት ያስፈልገናል

ለሰራተኛው ህዝብ፡- በሺዎች የኑሮ-ምንዳዎችን መፍጠር፣ በህብረት የታቀፉ ስራዎች የታደሱ ህንጻዎች፣ ወደ ንጹህ ኃይል ሽግግር፣ እና የህዝብ መጓጓዣ ማስፋፋት፣ ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ማድረግ እና ነጻ ማድረግ።

ከኮርፖሬሽኖች፣ ዋና ስራ አስፈጻሚ ባለስልጣናት [CEOs]፣ የንግድ ድርጅት ተደራዳሪዎች፣ ወይም ትላልቅ አልሚውች ዘንድ አንድ ሳንቲምም አልቀበልም። እኔ
የአማካኝ ሰራተኛ ምንዳ ብቻ ወደ ቤቴ እወስዳለሁ፣ ቀሪውን $130,000 ደሞዜን ለማህበራዊ ንቅናቄዎች እለግሳለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*

**የእጩው ስም፡-** ሎጋን ባወርስ [Logan Bowers]
**የዘመቻ ስም፡-** ሎጋን [Logan] ለሲያትል
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** https://www.votelogan.org/
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 3
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 360-797-9037
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ፍላጎቶችዎን የሚወክል እና ማህበረሰብዎን የሚያዳምጥ የምክር ቤት አባል ይገባዎታል። የመኖሪያ ቤት እጦት ችግር፣ ተመጣጣኝ ያልሆነ የመኖሪያ ቤቶች እና በከተማችን ውስጥ የእኩልነት አለመኖር ችግሮችን ለመፍታት በከተማው ምክር ቤት አዲስ አመራር ያስፈልገናል።

እኔ የጥቃቅን ንግድ ባለቤት ነኝ፣ ዕድሜ ልክ የሲያትል ነዋሪ እና ተከራይ ነኝ። ከተማችን በደንብ ሲያድግ ተመልክቻለሁ፣ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች እና ማህብረሰቦች ወደ ኋላ ቀርተዋል። ሁሉም ሰው ከሲያትል ብልጽግና ተጠቃሚ እንዲሆን እፈልጋለሁ፣ እናም ዕቅድ አለኝ።

ምክር ቤቱ የከለከለውን በአካባቢው ተስማሚ የአሰፋፈር ክምችት በመፍጠር ተመጣጣኝ ቤቶችን በሕጋዊነት ለማስመለስ እቅድ አለኝ።

አሁን ለ 12, 000 ሰዎች 6,000 የመጠለያ አልጋዎች ብቻ ስላሉን ማደሪያ የሌላቸውን ጎረቤቶቻችን ለማስጠለል እቅድ አለኝ።

ከ 1950 ጀምሮ ዘመን ኋላቀር በሆኑ ህጎች ምክንያት ለብቻ ተነጥለው የቆዩ መንደሮች እና ትምህርት ቤቶች ፍትሃዊነት ለመጨመር እቅድ አለኝ።

ለእኔ ለሎጋን ባወርስ ድምጽ ይስጡ፣ [Logan Bowers]፣ እና አንድ ላይ ሆነን የእኔን እቅድ ወደ ተግባር መለወጥ እንችላለን።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Pat Murakami
**የዘመቻ ስም:** Pat for Seattle
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** www.patforseattle.org
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 3
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206.383.3384
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

ጤና ይስጥልን የአውራጃ 3 መራጮች፡፡

ለ Seattle የከተማ አስተዳደር የምወዳደረው የተሻለ መስራት ስለምንችል ነው፡፡

አውራጃው ውስጥ ከ35 አመታት በላይ ኖሬያለሁ፤ ለ20+ አመታት የአካባቢ በጎ አድራጎት ሰራተኛ ነበርኩ፡፡ የ IT ስራ ባለቤት እደመሆኔ መጠን (30+ አመታት) ከተማ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ንግዶችን ረድቻለሁ በእግረመንገዴ ለመኖር በቂ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራ ለመፍጠር የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ከንቲባ Nickels ን ስደተኞች እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የንብረት ባለቤቶችን ንብረታቸውን በዝቅተኛ ዋጋ ለቤት ሰሪዎች እንዲሸጡ ለማስገደድ የሚታወቅ ቦታን ከመጠቀም አስቁሜያለሁ፡፡

ብመረጥ የሚከተሉትን ለማድረግ ቃል እገባለሁ፡

ስጋቶቻችሁን ለመፍታት ሁልጊዜ ለመገኘት፡፡
ከትላልቅ ቤት ሰሪዎች በተቃራኒ ለመቆም፡፡
የበለጠ በተመጣኝ ዋጋ ቤት መስራት በተለይ ልጆች ላላቸው ቤተሰቦች፡፡
ቤት ሰሪዎችን መሰረተ ልማት ላይ ተጽዕኖ ለፈጠሩበት ማስከፈል፡፡
የአደንዛዥ እጽ ማገገሚያ፣ የአዕምሮ ጤና እና የድጋፍ አገልግሎቶች እንዲአስፈላጊነቱ መስጠት፡፡
መጀመሪያ ለመጡ፣ መምህራን፣ ነርሶች እና የንግድ ሰዎች የቤት መግዣ መርሀግብሮችን መፍጠር፡፡
ለመኖር በቂ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራዎች መፍጠር፡፡
አነስተኛ ንግዶችን መደገፍ፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** ዘካሪ ዲወልፍ [Zachary DeWolf]
**የዘመቻ ስም፡-** ዘካሪ ዲወልፍ [Zachary DeWolf] ይምረጡ
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** electdewolf.com
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 3
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-395-5112
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

አሁን ውክልናችን ለሁላችንም እየሰራ ስላልሆነ እኔ ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Seattle City Council] እየተወዳደርኩ ነው። በመፍትሔዎች ላይ አተኩሮት ያለው አመራር ያስፈልገናል፣ እናም ሰዎችን ለመከፋፈል ሳይሆን ሁሉንም ለማዳመጥ ቁርጠኛ የሆነ ውክልና ይገባናል። የአሁኑ የሲያትል ትምህርት ቤት ቦርድ ዳይሬክተር [Seattle School Board Director] እንደመሆኔ ሁሉችንም ተማሪዎቻችን፣ መምህራኖቻችን እና ቤተሰቦቻችንን በመወከል በየቀኑ በመስራቴ ክብር ይሰማኛል። የ ኦል ሆም ኪንግ ካውንቲ [All Home King County] የፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ እንደመሆኔ መጠን የወጣቶችን ቤት የለሽነትን በማስወገድ እና እንደ የማስቀየስ እና የመከላከል መርሃ ግብሮችን በመሰሉ የተረጋገጡ መፍትሄዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ላይ ስራየን አተኩሬያለሁ። የካፒቶል ሂል ማህረሰብ ምክር ቤት [Capitol Hill Community Council] የቀድሞ ፕሬዚዳንት እና የሲያትል መኖሪያ ቤት ባለሥልጣን የቦርድ ኮሚሽነር [Board Commissioner for Seattle’s Housing Authority] እንደመሆኔ ለአካባቢዎቻችን፣ ለተከራይ መብቶችን እና ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት መፍትሄዎች ላይ ታግያለሁ። ይህንን ተሞክሮ ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Seattle City Council] አመጣለሁ። እንደ እርስዎ የምክር ቤት

አባልነቴ እኔ ከተማዎትን ለሁሉም ነረቤቶቻችን ተቀባይ፣ ዋጋው ተመጣጣኝ እና ለመኖሪያነት ተስማሚ እንድትሆን ለማድረግ እሰራለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም:-** Alex Pedersen
**የዘመቻ ስም:** Elect Alex Pedersen
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ፡** www.ElectAlexPedersen.org
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-502-9092
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

Alex Pedersen ለከተማ መስተዳደር የሚወዳደረው ተጠያቂነትን ለመጨመር ነው፡፡ Alex በመንግስት አስተዳደር ማስተርሱን ከሰራ በኋላ በክሊንተን አስተዳደር ወቅት በ U.S. መምሪያ፣ የቤቶች እና ከተማ ልማት ውስጥ አገልግሏል፡፡ የ Alex ስራ ልምድ በግል ዘርፉ ላይ የተመጣጣኝ ዋጋ ቤቶችን ለማገዝ ከ15 አመታት በላይ የገንዘብ ተንታኝ ሀላፊ መሆንን ያካትታል፡፡
Alex የበጀት ኮሚቴውን በሊቀመንበርነት ለመራው የከተማ አስተዳደር ፕሬዚደንት Tim Burgess የህግ ረዳት ሆኖ አገልግሏል፡፡ Alex በ2014 በመራጮች የጸደቀው የ Seattle የቅድመ-ትምህርት ከፍተኛ ጥራት መርሀግብር ህግ ቀርጿል፡፡ Alex የነርስ ቤተሰብ ጥምረቶችን፣ (Nurse Family Partnership) አነስተኛ ገቢ ያላቸው እናቶች እና ልጆቻቸውን የሚያበረታታ ማስረጃ ተኮር መርሀግብሮችን በገንዘብ ለማገዝ ጥረቶችን በዋናነት መርቷል፡፡

ለማህበረሰቡ ችግሮች እና የ Northeast Seattle አነስተኛ ንግዶች አስፈላጊውን ትኩረት ለማምጣት Alex ላለፉት 5 አመታት የአካባቢው ጋዜጣ አሳትሟል፡፡

የ Alex ባለቤት ተወልዳ ያደገችው Seattle ውስጥ ሲሆን ከአስርተ አመታት በላይ ልጆቻቸውን ያሳደጉት Candy Cane Lane አካባቢ ነው፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም:-** ካቲ ተትል [Cathy Tuttle]
**የዘመቻ ስም:-** የካቲ ተትል [Cathy Tuttle] ጓደኞች
**የዘመቻ ድረ-ገጽ:-** http://cathy4council.org/
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር:-** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር:-** (360) 362-9739
**የእጩ ማስተዋወቂያ:-**

ከምወደው ከተማ ውስጥ ማርጀትን እወዳለሁ። የእኔ ልጆች እና ሁሉም የእኛ ልጆች ደስተኛ ሆኖ መኖርን፣ ምርታማ ህይዎትን እዚህ እንዲኖሩ እንዲችሉ እፈልጋለሁ። የእኔን ሁለት ልጆች ዛሬ በምኖርበት አንድ አይነት የዋሊንግፎር ድ ቤት ውስጥ ነው ያሳደኳቸው።

ውሳኔያችን የእኛን የወደፊት እጣ ፈንታ ባልታሰበ ፍጥነት እና ውጤት በሚቀርጽበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። እኔ መርዳት እችላለሁ።

በሲያትል ውስጥ ህዝብን በማገልገል፣ ከእቅድ ኮሚሽን [Planning Commission]፣ እና ከሲያትል መናፈሻ [Seattle Parks] ጋር 40 መናፈጻዎች እና የማህረሰብ ማዕከሎች ፕሮጀክትቶችን በማስተዳደር የ 30 ዓመት ተሞክሮ አለኝ።

በመቀጠልም የአየር ንብረት እና የጎዳና ደህንነትን ለማስጠበቅ የ 350 ሲያትል [350 Seattle] እና ስያትል መንደር አረንጓዴመንገድ [Seattle Neighborhood Greenway] ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን መስርቻለሁ።

የእናንተን ድጋፍ ለማግኘት በምሰራበት ውቀት ሃሳብዎችዎን ለመስማት በጣም ጓጉቻለሁ። እንደ እርስዎ ተወካይ ድምጽዎትን ወደ ከተማው ምክር ቤት በማምጣት ለመቀጠል ቃል እገባለሁ።

በአክብሮት የእርስዎን ድምጽ፣ ቫውቸሮችዎን፣ እና በሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Seattle City Council] እንዳገለግልዎ የእርስዎን ድጋፍ እጠይቃለሁ።

*እ ፕ ህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Emily Myers
**የዘመቻ ስም፡-** የ Emily Myers ማየርስ ጓደኞች
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ፡-** https://emilyforseattle.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 360-559-1486
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ኢሚሊ ማየርስ (Emily Myers) ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት Seattle የምትወዳደር ሳይንቲስት እና የሰራተኞች አደራጅ ነች። በ Washington ዩኒቨርሲቲ የ Parkinson በሽታ ለማጥናት ከምታበለጽጋቸው መሳሪያዎች በተጨማሪ የእርሱ ህብረት UAW4121 የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ናት፣ የ MLK የሰራተኛ ምክር ቤት (Labor Council) ወኪል፣ የ 500 ሴት ሳይንቲስቶች (Women Scientists) መሪ፣ የዋሽንግተን ሳይንስ ፖሊሲ ኔትዎርክ (Washington Science Policy Network) መስራቾች አንዷ፣ እና የቀድሞው ፕርሰንት ኮሚቴ ኦፍሴር በ 43ኛ ዲስትሪክት ዲሞክራትስ ናት። ኢሚሊ በሰራተኛ፣ ቤተሰቦች እና በይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ ማህረሰቦቻችን ማዕከል ያደረጉ ርህራሄ አዘል፣ በማስረጃ-የተመሰረቱ ፖሊሲዎች Seattle ያስፈልጋታል ብላ ታምናለች። ኢሚሊ ለመኖሪያ ቤት ለሁሉም፣ ተመጣጣኝ የህጻናት እንክብካቤ እና ቅድመ ትምህርት፣ የጾታ የደመዋዝ ክፍተትን ለማጥበብ የተሻለ ክፍያ እና ጥቅማ ጥቅሞች፣ እና የእኛን የካርቦን ለቀት ዱካ ለሚቀንሱ የከተማ ልማት እና መጓጓዣ ትታገላለች። የእርስዎን የዴሞክራሲ ቮቸሮች (democracy vouchers)፣ በጎ ፈቃደኝነት ቃል ይግቡ ወይም በእርሷ ድረ ገጽ emilyforseattle.com የበለጠ ይወቁ።

*እ ፕ ህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Ethan Hunter
**የዘመቻ ስም:** Ethan Hunter 4 Seattle City Council
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** https://hunter4seattlecitycouncil.com/
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር:** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር:** (206)-535-5733
**የእጩ ማስታወቂያ:**

Ethan Hunter ለ Seattle 4ኛ አውራጃ የከተማ አስተዳደር ለመመረጥ የሚወዳደረው ለ Northeast Seattle ነዋሪዎች በይበልጥ ለሚመለከታቸው ጉዳይ ካለው ስሜት የተነሳ ነው፡ የከተማችንን ቤት አልባ እና በጣም ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች መርዳት፣ የከፍተኛ ትምህርትን የበለጠ ተደራሽ ማድረግ፣ የጾታ እና የዘር የክፍያ ልዩነቶችን ማስተካከል፣ የህዝብ መጓጓዣን ወጪን ባገናዘበ መልኩ ማስፋፋት እና አካባቢያችን መጠበቅ፡፡ ለውጥ የሚያመጡ ወደስራ የሚቀየሩ እቅዶችን ለመፍጠር የከተማ አስተዳደር አባላት፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች እና የአካባቢያዊ ንግድን ለማስተባበር ዝግጁ ነው፡፡ Ethan የ Seattle የህዝብ ት/ቤት ውጤት እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎቻችን እና አስተማሪዎቻችን የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በልዩ ሁኔታ ይረዳል፡፡ ከሚሰራው-መደብ የመጣ ተማሪ እንደመሆኑ መጠን የ Northeast Seattle ሰዎችን የሚሰራ-መደብ ለመወከል በልዩ ሁኔታ ብቁ ነው፡፡ Ethan የሚኖረው በ U-አውራጃ ነው፡፡

Castro እና Jose ከሚባሉ ውሾቹ ጋር ጊዜ ማሳለፍ፣ Seahawks እና Mariners games ማየት እና ለፖለቲካ ዘመቻ የበጎ አድራጎት ስራ መስራት ይወዳል፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር ላይ አይሳተፉም፡፡*

**የእጩው ስም፡-** Frank Krueger
**የዘመቻ ስም፡-** ፍራንክ ክሪገር [Frank Krueger] ይምረጡ
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** https://votefrank.org
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-536-7853
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
እኔ በዉሊንግፎርድ [Wallingford] የትንሽ ንግድ ስራ ድርጅት ባለቤት እና ተከራይ ነኝ፣ እና ገቢያቸው ምንም ይሁን ሲያትል ማንኛውም ሰው ሊኖርባት የሚችል ከተማ ላደርጋት እፈልጋለሁ። የሰራተኛ መደብ ውስጥ ባሉ የሞተር መኪናዎች ላይ በሚሰራ ቤተሰብ ነው ያደኩት እና ጠንክሮ መስራት እና ለማህረሰብ መልሶ ማበርከትን ተምሬበታለሁ።

ከብዙ ሰዎች ጋር ለመማር እና ለመስራት እድሉ ነበረኝ፦ ከመሃንዲሶች እስከ ማህበራዊ ሰራትኞች እስከ መርከበኞች እና በመሃል ያሉትን ማንኛዎችንም። በሲያትል ውስጥ ከተለያዩ ሰዎች እና ሃሳቦች ጋር አድጌያለሁ፣ እና ሌሎችም መቻላቸውንም ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ሕይወቴን ሙሉ ብዝሃነትን እደግፋለሁ። በንግድ ስራየ በኩል አዲስ መጤዎችን ቀጥሬያለሁ እንዲሁም አዲስ አሜሪካዊያን ለመሆን የአሜሪካ የህግ ስርዓት መከተል እንዲችሉ ረድቻቸዋለሁ።

እያንዳንዱ ግለሰብ እሴት አለው እና እያንዳንዱ ሰው መደመጥ ይገባዋል። እኔ አዳምጣለሁ። በከተማው ምክር ቤት [city council] ድምጻችሁን ስለማሰማ የእኔ ልምድ እና የስራ ስነምግባር ሲያትልን በደንብ እንደሚያገለግል አውቃለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Joshua Newman
**የዘመቻ ስም:** Vote Joshua Newman
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** votenewman.com
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር:** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር:** 206-963-2397
**የእጩ ማስታወቂያ:**
Seattle ሲያድግ ለወደፊት ራዕይ እሴቶቻችንን እንደማህበረሰብ የሚያገናኙ መሪዎች ያስፈልገናል፡፡ የከተማ መስተዳደሩ ለሚያገለግለው ህዝብ ተጠያቂ እና ተደራሽ ሆኖ ለነዋሪዎቻችን ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ Joshua Newman Seattle ውስጥ ለሁለት አስርተ አመታት ኖሯል፤ አሁን አራት ልጆቹን ከሚስቱ Emily ጋር እያሳደገ ነው፡፡ Joshua የቦይንግ ኢንዱስትሪያል ኢንጂነር እና የቀድሞ የ Maple Leaf ማህበረሰብ ኮሚቴ ፕሬዚደንት እና የረዥም-ጊዜ የሽግግር ተከራካሪ እንደመሆኑ መጠን ለአካባቢያችን ይታገላል፣ ለመኖር በቂ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራዎችን እና አካባቢያችንን ይጠብቃል እንዲሁም የተመጠጣኝ ዋጋ እና የቤት ችግር የሚያመጣውን ጉዳት ለማስቀረት ያለድካም ይሰራል፡፡ በህይወቱ በሙሉ የሰራው ሰዎችን በማሰባሰብ ችግር ለመፍታት ነው፡፡ ሊጋራ የወደፊት ኑሯችን በአሁን ሰአት Seattle በትክክል የሚፈልገው ነው፡፡ Joshua በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር በመሳተፉ ኩራት ይሰማዋል እንዲሁም የእርስዎን የምርጫ ድምጽ በማግኘቱ ክብር ይሰማዋል፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** Sasha Anderson
**የዘመቻ ስም:** Sasha For 4
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ:** sashafor4.org
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 4
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-228-6845
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

ጤናይስጥልኝ Sasha ነኝ፡፡ የ12 አመት የአውራጃ 4 ነዋሪ ነኝ፣ የ Greenlake አዘውታሪ እና ከእጮኛዬ ጋር ቤት ለመግዛት የማስብ ተከራይ ነኝ፡፡

የምሰራው የህዝብ አገልገሎት ላይ ነው፤ በአሁን ሰአት የምሰራው በምመራው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የጥናት መርሀግብር ውስጥ ታላላቅ ወንድሞች ታላላቅ እህቶች (Big Brothers Big Sisters) ጋር ነው፡፡ የከተማችን ወጣቶች እውቀት እና እምቅ ሀይል ማየት ያስደስተኛል፤ በመሆኑም የበለጠ ፍትሀዊ Seattle ለእነሱ ለመፍጠር ዝግጁ ነኝ፡፡

አውራጃ 4ን ለማገልገል የምወዳደረው ከተማችን በፍጥነት እያደገ ስለሆነ እና ከእድገታችን ሁሉም ነዋሪ መጠቀሙን ለሚያረጋገጥ በጋራ ለመስራት ዝግጁ የሆነ ብቃት ያለው መሪ ስለሚያስፈልገው ነው፡፡ በየእለቱ ወደስራዬ የማመጣው አመራር አይነት ይህ ነው፤ ወደከተማ አስተዳደር ማምጣት እቀጥላለሁ፡፡

ይህ ዘመቻ የእርስዎን ድምጽ እና የእኔን ልምድ ወደከተማ አስተዳደሩ ማምጣት ነው፡፡ የምወዳደረው እንደጎረቤትዎ እና ጠበቃዎ ነው፡፡ አብረውኝ በመሆን የተሻለ ነገር በጋራ እንገንባ!

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** Alex Tsimerman
**የዘመቻ ስም፡-** አሌክስ ለ አሜሪካ
**የዘመቻ ድረ ገጽ፡-** AlexforAmerica.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 5
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-324-6264
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

<u>ክብርና ሞገስ ለሀገራችን</u> (21 ነጥቦች)

አሌክስ ሺመርማን [Alex Tsimerman]፣ የሲያትል እጩ ይህ እቅድ ለህዝቡ በዓመት 2 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያመጣ ያምናል።

1. ክራይ - 50% አፓርትማዎች በዓመት ከ $40,000 በታች ለሚያገኙ ሰዎች እና ክራይም ከገቢ 30% በላይ ሊሆን አይችልም። ለገንቢዎች እና አከራዮች ግብሮች አይኖራቸውም። በዚህ ለውጥ ቀሪው 50% ሰዎች የደሞዛቸውን 30% ይከፍላሉ እና ሁሉም ሰው በአሜሪካዊያን መመዘኛ ልክ እኩል ይሆናል።

2. ከ $100 ላነሱ ሸያጮች ግብሮች ይቁሙ – ከ $100 በታች ለሆነ ማንኛውም ነገር ግብር አይኖረውም…ሚሊዮነሮች በርካታ የግብር እፎይታ አላቸው። ድሃዉ እና መካከለኛው መደብ ተመሳሳይ ሊኖራቸዉ የሚገባቸዉ ጊዜ ነው።

3. የኮርፖሬት ቁጥጥር ይቁም – እንደ አማዞን [Amazon] እና ቨልከም [Vulcom] የመሰሉ ኮርፖሬሽኖች መግባታቸውን ማስቆም እና እነዚህን ኩባንያዎች ከመሃል ከተማ ማስወጣት። ይህም በርካታ የከተማ እና የመጓጓዣ ችግሮችን ሊፈታ ይችላል።

4. አባካኝ፣ ትልቅ ፕሮጀክቶች እና ንዑስ ተቋራጮችን ማስቆም – ST3 ይቁም።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*

**የእጩው ስም፡-** Ann Davison Sattler
**የዘመቻ ስም፡-** የ Ann ጎረቤቶች
**የዘመቻ ድረ ገጽ፡-** NeighborsforAnn.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 5
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-775-8838
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

በከተማዋ በውስጥ ከሃያ አመታት ያለፈ ና በአምስት በተለያዩ የሲያትል ስፍራዎች ኖሬያለሁ። እኔ የሁለት ልጆች እናት፣ የነጻነት አቀንቃኝ እና ጠበቃ ነኝ። Seattle ውስጥ ትንሽ የህግ ሙያ አገልግሎት መስጫ አለኝ እና በ ዩደብሊው ኮንቲነም ኮሌጅ (Continuum College) አለም አቀፍ ንግድ ህግ ትምህርት ክፍሎችን አስተምራለሁ።

Seattle ውስጥ በሚገኘው የሴንትራል ኤሪያ ዩዝ አሶሴሽን (Central Area Youth Association) ማስጠናትም ሆነ ወይም የወጣት እግር ኳስ ማስልጠን በጎ ፈቃደኝነት፣ የማህረሰብ አገልግሎቶች ለእኔ አስፈላጊ ናቸው። በእኔ አካባቢ የት/ቤት ቦርድ፣ በረንዳ አዳሪዎች፣ ቀደም ብለው ታስረው ለነበሩ የማገገሚያ ቤት፣ እና በውጭ ሀገር የሚገኝ የስደተኛ ካምፕ በበጎ ፈቃደኝነት ላይ በመሳተፍ ቆይቻለሁ።

የማህረሰቡ ቤት የለሽነት እና የመኖሪያ ቤት፣ የህዝብ ደህንነት ጥበቃ፣ እና ሱስ መከላከል/ማገገም እንዲሻሻል መጮኽ ለሃላፊነት እንድወዳደር አስገድዶኛል። ለነዋሪዎች ጭንቀቶች ምላሽ የሚሰጥ፣ ሃላፊነት የተሞላበት የህዝብ ገንዘብ አጠቃቀም፣ ቁርጠኛ የሆነ መሪ ጋር በዲስትሪክት 5 ውስጥ ትርጉም ያለው እድገት ይቻላል። እኔ የለውጥ ማምጫ መሳሪያ ለመሆን ቁርጠኛ ነኝ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*

**የእጩው ስም፡-** ዲቦራ ጁሬዝ [Debora Juarez]
**የዘመቻ ስም፡-** ዲቦራ [Debora] ለ ዲስትሪክት 5 [District 5]
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.deborajuarez.com
**የከተማ ምክር ቤትዲስትሪክት ቁጥር፡-** 5
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-258-5767
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ሰሜን ሲያትል ለረጅም ጊዜ ችላ በመባሏ ምክንያት የምክር ቤት አባሏ ዲቦራ ጁሬዝ በ 2015 ተወዳድራለች። እንደ የህግ ባለሙያ፣ ዳኛ እና እናት፣ የ 31 ዓመት ዲስትሪክት 5 [District 5] ጎረቤት በመሆን ያኗትን ተሞክሮ በመጠቀም፣ ነዋሪዎችን አድምጣለች፣ ለ D 5 ታግላለች እና የሚከተሉትን ጨምሮ ተጨባጭ ውጤቶችን አምጥታለች፤

- $18 ሚሊዮን አዲስ የ ሌክ ሲቲ ማህረሰብ ማዕከል [Lake City Community Centre]
- በሲያትል ማዕከል ውስጥ $1.6 ቢሊዮን የአለም ደረጃ የጠበቀ የውድድር ቦታ፣ ግብር ከፋዮች ምንም ወጪ ሳያወጡ
- የኖርዝጌት እግረኛ-ቢስክሌት ድልድል ሙሉ በሙሉ የገንዘብ ድጋፍ ያቀረበ
- በ$80 ሚሊዮን NHL የማሰልጠኛ ተቋም በ ኖርዝጌት
- 1200 አዲስ አቅምን ያማከለ መኖሪያ ቤቶችን ወደ D5 ያመጣ

የምክር ቤት አባሉ ጁሬዝ መንገዶች የእግረኛ መንገዶችን በመገንባት፣ ፖሊሶችን በመጨመር እና የ አሰሳ ቡድን እና የሕግ አስፈጻሚ ኢጋዥ አስቀያሽ [Navigation Team and Law Enforcement Assisted Diversion (LEAD)] በማስፋፋት ጎዳናዎቻቸን የበለጠ ደህንነታቸው የተጠበቀ አድርጋለች። መኖሪያ የሌላቸውን ጎረቤቶቻችንን ለመርዳት በሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ለትርፍ ላልተቋቋሙ ድርጅቶች አስገኝታለች። እሷም የ 130ኛው ጎዳና የቀላል ባቡር ጣቢያ 7 አመት ቀደም ብሎ እንዲከፈት ትግል እያደረገች ነው።

ግን አሁንም ገና ተጨማሪ የሚሰሩ ስራዎች አሉ። እባክዎ ለምክር ቤት አባሏ ጁሬዝ ድምጽ ይስጡ!

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** John Lombard
**የዘመቻ ስም:** Friends of John Lombard
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ፡** votejohnlombard.com
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 5
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-486-0439
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

ለከተማ አስተዳደር የምወዳደረው ተሳትፎ ያለው፣ ምላሽ የሚሰጥ አመራር ለአውራጃ 5 ለማምጣት፤ ከተማው እንዲያድግ እና ለቤት አልባዎች የተመጣጠ፣ተግባራዊ የሚሆን እና ውጤታማ ምላሽ እንዲሰጥ ለማገዝ እና ከተማው ሌላ ተቀዳሚ ጉዳዮች ላይ ማለትም የህዝብ ደህንነት፣ ተመጣጣ ዋጋ ያለው ቤት እና መጓጓዣን ጨምሮ ትኩረት እንዲያደርግ ለማገዝ ነው፡፡ ለ17 አመታት የአውራጃ 5 የማህበረሰብ መሪ ነኝ፤ የ Thornton Creek Alliance ፕሬዚደንት፣ የ Northgate Stakeholders Group ተጽዕኖ ፈጣሪ መሪ፣ የሰሜን ዲስትሪክት ምክር ቤት (North District Council) የጋራ ሊቀመንበር እና የአውራጃ 5 ማህበረሰብ ትስስር ዋና አዘጋጅ ሆኜ አገልግያለሁ፡፡ የ Northgate ነዋሪ ነኝ፤ የ Lake City ማህበረሰብን ፍላጎት እና ምኞት በጣም አውቀዋለሁ፤ ለበርካታ አስርተ አመታት የተተወውን ለማስተካል በ Aurora ሁለቱም በኩል ከሚገኙ ማህበረሰቦች ጋር መስራት እፈልጋለሁ ተከራይ ነኝ፤ የአውራጃ 5ን ብዙሀነት አከብራለሁ እንዲሁም ያስደስተኛል፤ ከአዲስ ግንባታ መልቀቅ/መፈናቀልን በዋናነት እዋጋለሁ፡፡ የእርስዎን ዲሞክራሲ ቮውቸር ባገኝ ደስ ይለኛል፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** ማርክ መንዴዝ [Mark Mendez]
**የዘመቻ ስም፡-** ማርክ መንዴዝ [Mark Mendez] ማርክ መንዴዝ [Mark Mendez] ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Seattle City Council]
**የዘመቻ ድረ ገጽ፡-**
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 5
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-551-3320
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

***ሰሜን ሲያትል\ ነዋሪዎች ለዲስትሪክቱ 5 አዲስ ራዕይ እና ተጠያቂነት ዝግጁ በመሆናቸው ምክንያት ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Seattle City Council] እየተወዳደርኩ ነው።*** እኔ የተወለድኩት እና ያደግሁት በሲያትል ውስጥ ሲሆን ለ 41 ዓመታት ሌክ ሲቲ [Lake City] አጎራባች በሆነችው ዲስትሪክት 5 [District 5]ውስጥ ኖሪያለሁ። በበርካታ የአካባቢያዊ እና ዓለምአቀፍ በእኩል ፍትሃዊነት ጉዳዮች ላይ ሕይወቴን እና ሙያዬን አሳለፌያለሁ። በሲያትል እና ዲስትሪክት 5 [District 5] ውስጥ ያሉ ታላላቅ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ከተለያዩ የሰዎች እና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ነገሮችን 'እንዲያከናውኑ በማድረግ' ምዝግብ አለኝ። ለበርካታ አትራፊ ያልሆኑ፣ ትምህርት እና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሠርቻለሁ፤ የሰሜን ዲስትሪክት ምክር ቤት [North District Council] ተባባሪ ሊቀመንበር ፣ ሌክ ሲቲ የጎረቤት አከባቢ ትብብር [Lake City Neighborhood Alliance] ቦርድ እና በሜድዎርክ ማህበረሰብ ጥበቃ [Meadowbrook Community Care]

ቦርድ ሆኜ ሰርቻለሁ። እኔ ከማህበረሰብ ቡድኖች እና ድርጅቶች ጋር አብሬ የሰራሁባቸውን ተመሳሳይ ስኬታማ ሞዴሎች በማምጣት በሁሉም ዲስትሪክት 5 [District 5]ተግባራዊ ማድረግ እፈልጋለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** *ታይላ ማሆኒ* [Tayla Mahoney]
**የዘመቻ ስም፡-** *ማሆኒ* [Mahoney] *ለ ሲያትል*
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** mahoneyforseattle.org
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 5
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-388-7328
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

የሲያትል ከተማ ምክር ቤት እጩዎትን ለመመርመር ጊዜዎን ስለሰዉ እናመሰግንዎታለን። በዲስትሪክት 5 [District 5.] ውስጥ የወደፊት ተውካይ ለመሆን የምወዳደር በመሆኔ ክብር እና ደስታ ይሰማኛል። እኔ ተወልጄ ያደኩት እዚህ ነው እና ስለ ከተማችን አስባለሁ። የሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Seattle City Council] የአዳዲስ አስተያየቶችን እንደሚያስፈልግ እና የእኛን ዲስትሪክቶች [Districts] ለመወከል ብቻ ሳይሆን የከተማችን በጠቅላላ የታደሰ ስሜት ለመደገፍ ነው።

ለውጥ ለማምጣት በሚያስችል የከተማ ምክር ቤት [city council] ውስጥ መሆን እፈልጋለሁ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የአደንዛዥ ዕፅ ቀውስ ሙሉ በሙሉ እየቀነሰ መሄዱን፣ እናም ከዚያ ጋር፣ የንብረት ወንጀሎች መቀነስ፣ እንዲሁም አንድ ሰው ያለ መጠለያ የሚቀርበትን ገጠመኝ ቀንሶ ማየት እፈልጋለሁ። የወንጀል መደጋገምን ሁኔታ ለመቀነስ እና የመኖሪያ ቤት እጦትን ለመከላከል ማኅበራዊ አገልግሎቶች ጨምረው ማየትን እፈልጋለሁ። ይህንም ግብሮች በከፍተኛ ሳያሻቅቡ ማሳካት እፈልጋለሁ። አሁን እያጋጠሙን ላሉት ችግሮች በተጨባጭ እውነታ ላይ በተመረኮዙ፣ በደንብ ምርምር በተደረገባቸው መፍትሄዎች ተግባራዊ ማድረግ እፈልጋለሁ።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*

**የእጩው ስም፡-** *ዳን ስትራውስ*\
**የዘመቻ ስም፡-** *ሲያትል ለ ስራውስ*\
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** seattlefordanstrauss.org
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** (205) 569-8775
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

በ ቦላርድ\ የተወለደው እና ያደገው፣ አገልግሎትት ለዳን ዋናው ቁም ነገር ነው።

በአሜሪካ ውስጥ በአነስተኛ ገቢ ባላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ከ AmeriCorps ጋር ከአደጋ ዕርዳታ እስከ ድህረ-ትምህርት መርሃ-ግብሮች በሚሰሩ ፕሮጀክቶች ላይ በመሥራት አገልግሏል።

ዋና ዋና የህዝብ ጉዳዮችን ወስዶ ተሳክቶለታል። በኦሊምፒያ\ ላይ በከፍተኛ የስጋት መከላከያ\ ሕግ ላይ እና በጠመንጃ ሁከት መከላከያ ፖሊሲዎች አፈፃፀም ላይ ይሠራ ነበር።

ወደ አስር አመታት የህግ አውጭነት ልምድ፣ ዳን ለውጦችን እንዴት ማምጣት እንደምቻል ያውቃል። ችግሮችን ለመፍታት ሁሉንም የአስተዳደር እርከኖችን አንድ ላይ አመጥቷል። ከግዛት፣ ካውንቲ፣ ከተማ እና ማህበረሰብ ቡድኖች ጋር በማቀናጀት በትራንስፖርት ፕሮጀክቶች በገንዘብ ለመደገፍ፣ አረንጓዴ የግንባታ ኮዶችን ለማዘጋጀት እና መናፈሻዎቻችንን ለማሻሻል ይሠራል።

ዳን ለዲስትሪክት (ቀጠና) 6 ነዋሪዎች ድምጽ ይሰጣል። የማኅበረሰብ አገልግሎቶችን ቅድሚያ ይሰጣል፣ የአካባቢውን ቢሮ ይከፍታል፣ የቤት የሌሽነት እና የመኖሪያ ቤት ቀውስ መፍትሔ ይሰጣል እንዲሁም ለሁላችንም የሚሰራ የመተላለፊያ አውታረመረብ ይገነባል።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ጀርሚ ኩክ [Jeremy Cook]
**የዘመቻ ስም፡-** ጀርሚ ኩክ ለሲያትል ከተማ ምክር ቤት [Jeremy Cook for Seattle City Council]
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** cookforcouncil.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206.664.1293
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ጀርሚ [Jeremy] በሲያትል ውስጥ ከአስር አመት በበለጠ ምስል ነዳፊ ሆኖ እየሰራ ኗሯል። ሲያትል የምትሰጠውን በርካታ አዝናኝ እና አስደሳች እንቅስቃሴዎች ይደሰታል። የንስር ስካውት[Eagle Scout] ነው እና ከኖዝዌስት ኮሌጅ [Northwest College] በኮሚኒኬሽን ዲግሪ አለው።

እርሱ ለከተማ ምክር ቤት [city council] እየተወዳደረበት ያለው ምክንያት ሲያትል የገጠማትን በርካታ ችግሮች ለመፍታት ነው። በሌሎች ወይም በንብረታቸው ላይ ወንጀል የሚፈጽሙትን ሰዎች በማሰር ያምናል። ጀርሚ [Jeremy] አብላጫ የወንጀል ፈጻሚዎችን በመልሶ ማገገሚያ ለመመለስ መስራት ይፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ ይህ በእስር ላይ እያሉ የመድሃኒት ህክምና እና ክትትል ያለበት ለስራ መለቀቅ ያስፈልገዋል።

ጀርሚ [Jeremy] ሲያትልን በበለጠ እንደ አቅም የሚኖርባት ቦታ ለማድረግ ይፈልጋል። ይህ እንዲሆን ከተማዋ ሀብቶቿን በጥበብ ልትጠቀምባቸው ይገባል። አልሚዎች ለባለድርሻዎቻቸው እንደሚያደርጉት ከተማም ለዜጎቻቸው ይህን ማድረግ ይኖርባቸዋል፣ የከተማዋች ግብ ከትርፍ ይልቅ በአቅም የሚኖርበት መኖሪያ ነው።

ለቮቸሮዎችዎ እና ድምጽዎ እባክዎ ጀርሚ [Jeremy] ያስቡ።

እናመሰግናለን፣

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Joey Massa
**የዘመቻ ስም፡-** ጆይ ማሳ [Joey Massa] ለ እድገት
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.MassaforProgress.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-717-5675
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ጆይ ማሳ [Joey Massa]፣ የዋሽንግተን ብሄራዊ የክብር ዘብ ሰራዊት [Washington Army National Guard] ሆኖ ያገለገለ እና ከካንሰር በሽታ የተረፈ፣ የሲያትል የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት 6 [Seattle City Council District 6] ቦታ እጩ ነው። ማሳ [Massa]፣ የሚኖረው ከባለቤቱ ጋር በቦላርድ [Ballard] ውስጥ ሲሆን፣ ውድድሩን የተቀላቀለው በማበብ ላይ ባለች የ 21-ክፍለ ዘመን ከተማ የህዝብ ጤና እና ደህንነት፣ መጓጓዣ እና የሕይወት ጥራትን በተጨባጭ አቀራረብ ለማሻሻል ነው።

ማሳ [Massa] “የእኛ ከተማ ከጊዜ ወደ ጊዜ ባረጁ እና በተሰበሩ መሳሪያዎች ችግሮችን ለመጠገን ደጋግማ ሞክራለች” ይላል። “በዚህ ዲስትሪክት ውስጥ ዓመታትን እንደማሳለፌ፣ በርካታ የኖርዝዌስት ሲያትል [Northwest Seattle] ጎረቤቶቼ የቤት አልባነት ችግሮችን ለመፍታት፣ የህዝብ መጓጓዣን ዳግም ለማጤን፣ እና የመጀመሪያ ምላሽ ሰጪዎችን ለማጎልበት ያለኝን ጠንካራ ፍላጎት እንደሚቀላቀሉኝ አውቃለሁ። በርካታ ፖለቲከኞች ራስን አሳልፎ መስጠትን በመተው ወደ ሀብት እና ሃይል ያደሉበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። የአገልጋይ አመራር፣ ዲፕሎማሲ እና ተጨባጭ የከተማ አስተዳደር የሚያመጣ ሰው ያስፈልገናል፣ ያንን ማድረግ እንዲያስችለኝ የመራጮችን አመኔታ ለማግኘት ጠንክሬ እሰራላሁ።”

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ጆን ፒፕልስ [John Peeples]
**የዘመቻ ስም፡-** ፒፕልስ [Peeples] ለ ሲያትል
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.peeplesforseattle.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** (206) 552-0872
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ጆን ፒፕልስ [John Peeples] የአሁኑን የሲቪል እና የኢኮኖሚያዊ ከፍተኛ እምርታ ለሁሉም የከተማው ነዋሪዎች ከጥቅሙ እንዲቋደሱ ለማስቻል ለዲስትሪክት 6 [District] ከተማ ምክር ቤት [City Council] እየተወዳደረ ነው። ሲያትል የእርስዎ ከተማ ናት። ሲያትልን በክብር፣ ደህንነት እና ብልጽግና አቅጣጫ በመጠቀም በእርስዎ ከተማ ምክር ቤት ላይ አውንታዊ ለውጦችን እናመጣለን። እርሱ የከተማዋን ሰፊ ችግሮች ለመፍታት በደንብ ተጢነው የተተነተኑ ስልቶችን ይዞ የሚመጣ መሃንዲስ ነው።

ጆን [John] በህዝብ ደህንነት ተል ዕኮው ውስጥ የህግ አስከባሪዎችን ይደግፋል። የአእምሮ ጤና እና ንጥረ ነገርን ያላግባብ የመጠቀም
ችግሮች፣ ለቤት የለሽነት አስተዋጾ አድራጊዎች፣ ራስን እንዲጎዱ በመፍቀድ ሳይሆን በተገቢው የህክምና እንክብካቤ እና ማገገም ሊስተካከል ይገባዋል። ጆን \[John] በከተማችን ውስጥ ምንም አደገኛ የአደንዛዥ እጽ መወጊያ ጣቢያዎች አለመፈቀዳቸውን ያረጋግጣል። የማቋረጫ አከፋፈልን በመቃወም እና ሞንጎሊያ ድልድይን በመተካት ጎረቤቶቻችን ቤቶቻችው መድረስ እንዲችሉ ለማስቻል ይታገላል ።

እርሱ በቤት ስራ አጋዥ \[Homework Helper] መርሃ ግብር እና በቅርብም ዲፓርትመንት ኦፍ ኔቨርሁድስ ፒፕልስ አካዳሚ ኦፍ
እንጌጅመንት ጋር በጎ ፈቃደኛ ነው።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*

**የእጩው ስም፡-** Jon Lisbin
**የዘመቻ ስም:** Friends of Jon Lisbin
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ፡** jonlisbin.com
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** 206-794-5969
**የእጩ ማስታወቂያ፡**

ከ15 አመታት በላይ የ Ballard ነዋሪ እና የአነስተኛ ንግድ ባለቤት እንደመሆኔ መጠን በማህበረሰባችን ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ነበረኝ ለምሳሌ የ Salmon Bay K-8 የወላጅ አስተማሪ ድርጅት ዳይሬክተር፣ የ Ballard Little league አሰልጣኝ እና የቦርድ አባል እና ተልዕኮው የ Seattleን ፈጣን እድገት በማቻቻል የመኖሪያነት ሁኔታውን ማስቀጠል የሆነ የአካባቢ ተከራካሪ ቡድን የ Seattle Fair Growth ፕሬዚደንት፡፡ ለ Seattle የከተማ አስተዳደር የምወዳደረው

አካባቢያችንን ለማሻሻል እና እንደ ተመጣጣኝ የቤት ዋጋ፣ የቤት አልባነት እና ከከተማችን እድገት ጋር ሁኔታዎችን ማስተካከል የመሳሰሉ ዛሬ Seattleን የሚያጋጥመውን በርካታ ችግሮች ለመፍታት ነው፡፡ በዘመቻው ላይ አሁን ያለው የከተማ አስተዳደር የነዋሪዎችን ስጋት እንደማይሰማ ወይም የግብር ገንዘባቸውን በአግባቡ ስራ ላይ እንደማያውል ነዋሪዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡ ከተመረጥኩ ሁሉም ድምጾች መሰማታቸውን እና መከበራቸውን አረጋግጣለሁ፡፡ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር ላይ በመሳተፌ ኩራት ይሰማኛል፤ የእርስዎን ድምጽ ባገኝ ክብር ይሰማኛል፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** Kate Martin
**የዘመቻ ስም:** Put Kate On the Council
**የዘመቻ ድህረ-ገጽ፡** https://www.putkateonthecouncil.org/
**የከተማ አስተዳደር አውራጃ ቁጥር፡** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡** (206) 579-3703
**የእጩ ማስታወቂያ፡**
ጤናይስጥልኝ ነዋሪዎች እና ከ Green Lake እስከ Golden Gardens እንዲሁም ከ Blue Ridge እስከ Fremont ያላችሁ ንግዶች፡፡
አውራጃ 6 በከተማ አስተዳደር ውስጥ ውክልና አልነበረውም፡፡ እናስተካክለው፡፡

ለ33 አመታት የአውራጀ 6 ነዋሪ እንደመሆኔ መጠን ከ90ዎቹ ጀምሮ በአካባቢያዊ፣ በከተማ-ደረጃ እና የት/ቤት አውራጃ ጉዳዮች ላይ ያለ ያለእረፍት ተሳትፌያለሁ፤ እቅድ እና ቅርጽ አውጪ ስራዬም ውጤታማ የሚሆን የሚተገበሩ እና የፈጠራ ሀሳቦችን የመገንባት የአስርተ አመታት ልምድ ሰጥቶኛል፡፡ ውጤታማ ፖሊሲ እና ህግ ለማውጣት የሚያስፈልጉትን መተባበር እና ችግሮች ውስጥ "ጠልቆ ለመግባት" እጥራለሁ፡፡

ችግሮቻችን የተቸገሩ ሰዎች ወረርሺኝ፣ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ወንጀል፣ ስነ-ስርአት አልባነት እና ጥፋት እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ቤት እና የንግድ ቦታን ይጨምራሉ፤ እነዚህ አፋጣኝ ምላሽ ይፈልጋሉ፡፡

በአካባቢያችን እና በአነስተኛ ንግዶች ላይ ተገቢ ያልሆነ ወጪ፣ በአግባቡ ያልተያዘ እድገት እና ከላይ ወደታች የሚወርድ የህግ ጥቃቶችን እንደማስተካክል ይተማመኑብኝ፡፡

የእርስዎን ድጋፍ ባገኝ ደስ ይለኛል፡፡

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር እየተሳተፉ ነው፡፡*

**የእጩው ስም፡-** መሊሳ ሀል [Melissa Hall]
**የዘመቻ ስም፡-** Hall4Six
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.Hall4Six.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-708-4500
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ለተጨማሪ ሰዎች ቦታ መልቀቅ እያንዳንዱ ከተማ ውስጥ ፈታኝ የሆነ ነገር ነው፣ ነገር ግን ሲያትል የምትቀበለው እና የምትወጣው ተግዳሮት ሲሆን አካታች፣ ተቀባይ ቦታ በመሆኗ በራሷ ትኮራለች።ለተጨማሪ ሰዎች ቦታ መልቀቅ እያንዳንዱ ከተማ ውስጥ ፈታኝ የሆነ ነገር ነው፣ ነገር ግን ሲያትል የምትቀበለው እና የምትወጣው ተግዳሮት ሲሆን የምትኮራበት አካታች፣ ተቀባይ ቦታ መሆኗን መቀጠል አለባት። ሁሉም ዓይነት ሰዎች እንዲኖሩ ተጨማሪ ቦታዎች ያስፈልጉናል እና ወደዚያ ለመድረስ በግል መኪና ይዞታ የማይመካ መንገዶች ያስፈልጉናል። መልካም መሻሻሎችን አድርገናል ነገር ግን ይህ መወጣት ያለብን ከባዱ መካከለኛ ክፍል ነው ለውጦችን የምናደርግበት ነገር ግን ውጤቶችን ገና ያለየንበት፣ በማንኛውም ጊዜ አንድ ትልቅ ነገር በምትገነቡበት ጊዜ የምከሰት ነገር። በሌላ ጎን ትናንሽ ማህረሰቦች የሞሉባት ከተማ የምትፈልገው ነገር በቅርብ የምገኝበት ነው።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፦** ሰርጆ ጋርሺያ [Sergio Garcia]
**የዘመቻ ስም፦** ሰርጆ [Sergio] ለ ሲያትል
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፦** http://sergioforseattle.org/
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፦** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** 206-446-8968
**የእጩ ማስተዋወቂያ፦**

እኔ ሰርጆ ጋርሺ [Sergio Garcia]፣ የፊኒ ሪጅ ነዋሪ፣ እና ለቦላርድ/ፍሪሞንት [Ballard/Fremont] አካባቢ ተመድቤ የነበረ የፖሊስ መኮነን ነኝ። የከተማችን ማራኪነት፣ ልዩነትን፣ ተራማጅ እሴቶችን፣ ወደ ተፈጥሮአዊ ቅርብነት እና የእኛ አስተዳደር እና ሲቪል ማህበረሰብ ፈጠራ አቀራረብ ለመከተል ፈቃደኛ መሆናችን እወዳለሁ። ይህ ለሁላችንም፣ የፍልሰተኞቻችን፣ የስደተኞቻችንና LGBTQ ማህበረሰቦቻችን ጨምሮ የተሻለ ጥራት ያለው ህይወት ይፈጥራል። ከአካባቢያችን ነዋሪዎች፣ ከትንሽ የንግድ ድርጅቶች ባለቤቶች እና ቤት አልባዎች ጋር የመሰረትኩት ጓደኝነት ትልቅ ክብር እሰጠዋለሁ። በዴስትሪክቱ ስድስት [District Six] ውስጥ ያለ እያንዳንድ ሰው በየዕለቱ የሚያጋጥመውን ትግሎች እንዲረዳ አስችሎኛል። እንደ ፖሊስ፣ በድስትሪክታችን ፈተናዎች ፊት ለፊት እጋፈጣለሁ። የእነርሱን ስረመሰረት ምክንያቶች ይገቡኛል እና እነሱን ማሸነፍ እንደምንችል አውቃለሁ። እኛ እያጋጠሙን ያሉትን እጅግ በጣም ውስብስብ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ሚዛናዊ አቀራረብ በመያዝ በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉትን የሁሉንም ሰዎች የሕይወት ጥራት ማሻሻል ነው።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፦** ቴሪ ራይስ [Terry Rice]
**የዘመቻ ስም፦** ቴሪ ራይስ [Terry Rice] ይምረጡ
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፦** www.ElectTerryRice.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፦** 6
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** 206.799.5280
**የእጩ ማስተዋወቂያ፦**

እኔ ሃሰቦችን በተግባራዊነታቸው የምለካ፣ ተራማጅ እጩ ነኝ። በዲስትሪክት 6 [District 6] ውስጥ እንደሚገኙ አብላጫ ጎረቤቶቼ ቤት የለሽነት ያጋጠማቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጎረቤቶቼ ያስጨንቁኛል። ይህ የሰብዓዊ አደጋ ብቻ ሳይሆን የህዝብ ጤና እና የደህንነት አጠባበቅ አሳሳቢ ነገርም ነው። በአሁን ሰዓት የቤት የለሽነትን ያጋጠማቸው ሰዎች ቁጥርን ለመቀነስ ሊሰሩ የሚችሉ በጣም የተለዩ ነገሮች አሉ። በከተማችን ውስጥ ቤት የለሽነት ያጋጠማቸው 12,000 ሰዎች እና 6,000 አልጋዎች አሉን። ቤት የለሽነት ላጋጠማቸው ሰዎች አገለግሎቶችን ለመስጠት በአመት ወደ $200 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ይወጣል ይህን መሰል መሰረታዊ ችግሮችን ለማስተካከል ስኬታማ መንገዶችን ለማግኘት ብዙ ክፍተቶች አሉ። የመኪና ፍሰት መጨናነቅን ለመቀነስ እና የምናወጣውን የተቃጠል አየር ልቀት ለመቀነስ የቀላል ባቡር መስመሮች እየተገነቡ እያለ የሜትሮ አዉቶቡስ አገልግሎት ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ መቀጠል አለብን። በሲያትል ውስጥ የመኖሪያ ቤት ውጪን ጣራ መንካት መፍትሄ ለማምጣት እንዲያስችል የ ADUs ከተማ በሙሉ መፍቀድ እና የከተማ መንደሮችን መጠበቅ አለብን።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Andrew Lewis
**የዘመቻ ስም፡-** ሊውስ ለሲያትል Lewis
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.lewisforseattle.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-434-5871
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ስሜ አንድሪው ሊውስ እባላለሁ እና የበለጠ ተመጣጣኝ ክፍያ ያለው የመኖሪያ ቤት ግንባታ ላይ ፣ የሞንጎሊያ ድልድይ አንድ ባንድ መተካትን በማስጠበቅ፣ ለመሃል ከተማ ት/ቤቶች ለመታገል፣ እና በእኛ ከተማ መንግስት የአፈጻጸም የኦዲት ክትትል ለማስፋፋት ቁርጠኛ በመሆኔ ምክንያት በሲያትል ከተማ ምክር ቤት እርስዎን ለመወከል እየተወዳደርኩ ነኝ። የሰራተኛ መደብ ካለው ቤተሰብ ጋር Seattle ውስጥ አደኩኝ፣ እና Queen Anne ውስጥ ከሚገኘው ሴንተር ስኩል ተመርቄያለሁ። እኔ የዋሽንግተን ዩንቨርሲቲ፣ እንዲሁም የለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ፣ እና የካሊፎርኒያ ዩንቨርስቲ፣ የህግ ት/ቤት ኩሩ ተመራቂ ነኝ። አሁን በሲያትል ከተማ Seattle የጠበቃ ቢሮ ዐቃቤ ህግ ሆኘ እያገለገልኩ ነኝ።

በክብር እውቅና ተሰጥቶኛል፡- የኪንግ ካውንቲ የሰራተኛ ምክር ቤት፣ ተወካይ Gael Tarleton; fmr. የካውንቲ ምክር ቤት አባል ላሪ ፊሊፕስ፣\፤ የቀድሞ የካውንቲ ምክር ቤት አባላት Martha Choe, Heidi Wills, Nick Licata፣ እና በጣም በርካታ!

የበለጠ ከእርስዎ ለመስማት በጉጉት እጠብቃለሁ፣ እና የእርስዎን ድምጽ አገኛለሁ ብየ ተስፋ አድርጋለሁ!

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ዶን ሃርፐር\
**የዘመቻ ስም፡-** ዶን ሃርፐር\ ለ ሲያትል
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** donharperforseattle.com
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7-
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-351-5587
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
ዶን ሃርፐር በሾርላይን ውስጥ አድጎ በሲያትል ውስጥ ለ 49 ዓመታት ኖሯል። የደረጃ ሃላፊ / የመንገድ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሠርቷል፣ በኤሌክትሪሺያንነት እውቅ ባለሙያ ሲሆን ለ 28 ዓመታት የራሱ ኩባንያ በባለቤት ነው። ለ 21 ዓመታት በኩን አን\ ማህበረሰብ ምክር ቤት\ ውስጥ አገልግሏል፣ የመናፈሻዎች ኮሚቴ ሊቀመንበር ነው።

ዶን\ በከተማው ምክር ቤት ላይ ድምጽዎ ለመሆን እየተወዳደረ ነው። ምክር ቤቱ ዜጎችን እያዳመጠ አይደለም ወይም ቅድሚያ የሚሰጡትን ጉዳዮች በገንዘብ አይደግፍም። በ 1ኛ ጎዳና ላይ የፍሰት መስመሮችን ለማስወገድ የወደቀ የጎዳና መኪና ስርዓትን ለ “ማስተካከል” $ 286 ሚሊዮን ዶላር ማጥፋት አለብን? አይ፣ በተሻለ የሚሰሩ መፍትሄዎች አሉን።

ዶን\ የተረጋገጠ እና ተጠያቂነት ላላቸው ቤት የሌላቸው መርሃግብሮችን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንዳለብን ይረዳል። በአደገኛ እጾች ችግር ለተጎዱ ሰዎች፣ የሚያስፈልገን ህክምና እንጂ ነጻ ሄሮይን ወይም መርፌ ጣቢያን አይደለም።

ዶን\ በአዲሱ ጥልቅ የውሀ ውስጥ ወደብ የሚመጡትን የውሃ ዳርቻ ስራዎች ይደግፋል - እነዚህ ጥሩ የቤተሰብ የክፍያ ስራዎች ናቸው።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*

**የእጩው ስም፡-** ጂን በርስ
**የዘመቻ ስም፡-** የጂን በርስ\ ጓደኞች
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** https://geneforseattle.com/
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7-
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-**
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ጂን ቡሩስ በዳውንታውን ሲያትል ውስጥ ከአስር ዓመት በላይ የኖረ ጠበቃ ነው። ለአካባቢ ደኅንነት እና ለኢ=ዴሞክራሲያዎ ለሆነ የዳውንታውን ማእከላዊ የአካባቢያዊ ማሻሻያ ዲስትሪክት (LID)\ [Downtown Local Improvement District (LID)] የድምጽ ተቃውሞ 7 ኛውን ዲስትሪክትን\ ለመወከል ግልፅ ምርጫ አድርጎታል።

ጂን የከተማ አመራሩን ዜጎች አከባቢዎቻቸውን የህገወጥ መድሃኒት/እጽ ገበያ መሆናቸውን መ፤ ገዳቸውም በወንጀል የተሞሉ እንድሆኑ እና ቤቶቻቸውና ንብረታቸው ለጥበቃ የማይበቁ እንደሆኑ እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል.።

የሲያትል ነዋሪዎች ከተማዋ ለህዝብ የምትሰራ እንጅ ተቃራኒዉ አለመሆኑን የሚገነዘብ መሪ ይገባቸዋል። ጂን ትኩረት ወደ አንድ የከተማ አስተዳደር መሰረታዊ ተግባራት ላይ እንድመለስ ያደርጋል፦ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎችን መደገፍ፣ ቤት የለሽነት እና ለሱሰኝነት ሐቀኛ መፍትሄ ማፈላለግ፣ እንዲሁም የፊስካል ሃላፊነትን እና ተጠያቂነትን ማጉላት።

በከተማ ምክር ቤት ላይ የጂን ገለልተኛ ድምጽ ለሲያትል የሚያስፈልጋት ለውጥ ነው።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Isabelle Kerner
**የዘመቻ ስም፡-** ከርነር ለምክር ቤት Kerner
**የዘመቻ ድረ ገጽ፡-** kernerforcouncil.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206-271-1560
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

ተወልዳ ያደገችው Seattle ነው፣ የግል ት/ቤት ትታ የጋርፊልድ ከፍተኛ ት/ቤት ለመከታተል ስትገባ Seattle 'Running Start' መርሃ ግብር ውስጥ ተሳትፋለች እና የሲያትል የህዝብ ጽንፍ በሰፊው እይታ አዳብራለች ።

Kerner ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ባለው ከአሜሪካን ዩንቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስ ዲግሪ እና በስቱዲዮ ኪነ ጥበብ በንዑስ ተመርቃለች፣ ከርነር Banner & Witcoff የፈጠራ መብት የህግ ተቋም ውስጥ የዓለም አቀፍ የክስ ልዩ ባለሙያ ሆና ከመስራቷ በፊት በዋሽንግተን ስቴት ሴናተር፣ Maria Cantwell ተለማማጅ ተማሪ ሆና አገልግላለች።

Kerner የአሁኑን ምክር ቤት ፈጠራ ማነስ፣ ስምምነት ለመድረስ ፈቃደኛ አለመሆን፣ እና የ Seattle's ከፍተኛ ጫና ከሚያሳድሩ ማህረ-ኢኮኖሚያዊ እና የፖለቲካ ጉዳዮች ከሁሉም መጠን ካላቸው ንግዶች ጋር አብሮ መስራት አለመቻል። Kerner ቤት የለሽነት ወይም በረንዳ አዳሪነትን የመርከብ ማጓጓዣ የብረት ግዙፍ መያዣዎችን በአግባብቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ወይም ክፍት የሆኑ በከተማዋ ባለቤትነት ስር ያሉ መሬቶችን በመጠቀምወደ ጊዜያዊ መኖርያ ቤት በማሳደግ፣ ቤት የሌላቸው የፈጠሩትን ትርኪ ምርኪዎች እንዲያጸዱ በማድረግ ግለሰቦች ገንዘብ እንዲቀጥቡ እድሎችን ማቅረብ፣ እና ክህሎት ያላቸውን ሰራተኞች ለመጨመር የሚታገሉ ኩባንያዎች ጋር ሽርክና በመፍጠር ቤት የለሽነት ለመፍታት አቅዳለች።*እኚህ እጩ*

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር ላይ አይሳተፉም፡፡*

**የእጩው ስም፡-** ጃሰን ዊሊያምስ\
**የዘመቻ ስም፡-** ጃሰን ዊሊያምስ\ ምረጡ
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.electjasonwilliams.com
**የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7-
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 253-335-9564
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
እኔ የጋራ ብልጽግና ለማራመድ እና የህይወት ጥራትን ለማሳደግ ለከተማው ምክር ቤት እወዳደራለሁ።

የየል ኤምቢኤ እና የምርት ግብይት ባለሙያ እንደመሆኔ መጠን፣ ዕድገት የሥራ ዕድል ስለሚፈጥር እና ኢንቨስትመንት ስለሚስብ የሲያትል ኢኮኖሚ እንድያንሰራራ እፈልጋለሁ። ነገር ግን ሁሉም ሰው ከእድገቱ ተጠቃሚ እንደሚሆን ለማረጋገጥ የበለጠ ማድረግ አለብን። እዚህ ትምህርት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው። ለሁሉም ተደራሽ ዋጋዉ አቅምን ያማከለ፣ ከፍተኛ-ጥራት ያለው የቅድመ ትምህርት ማቅረብ አለብን ምክንያቱም እያንዳንዱ ህጻን በህይወቱ ፍትሃዊ እድል እና ስራ ይገባዋል።

ከተማችን እያደገ ሲሄድ፣ ለተሻሻለ የህይወት ጥራት የመሰረት ስራ መጣል ደግሞ አለብን። ሁሉም ሰው አከባቢያችን፤ በህላችንና ህዝባዊ ስፍራዎችን ቅርጽ በማስያዝ ድምጽ አንድኖረዉ እያደረግን እነኛን ሲያትልን ልዩ የሚያደርጉ መሬቶች፤ የዉሃ መንገዶች፤ እና ታሪካዊ ስፍራዎችን መጠበቅ አለብን።

በአካባቢያዊ መስተዳደር ላይ እምነትን ካሳደርን ብቻ ነው ይህ ህይወት ያለው፣ ሁሉን ያካተተ ወደፊት ሊሆን የሚችለው። ይህም በተሻለ ሁኔታ ማዳመጥ፣ ተጠያቂነትን ማጎልበት፣ እና የየቀኑን አስቸጋሪ የሆኑ ተግዳሮቶችን በአስቸኳይ መፍታት ይጠይቃል - ቤት የለሽነት፣ የዋጋ አቅምን ያማከለ አለመሆን፣ እና ነጭ ያልሆኑ ሰዎች መዋቅራዊ እኩልነት ማጣት።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ጂም ፑግል [Jim Pugel]
**የዘመቻ ስም፡-** የጂም /[Jim] ጓደኞች
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** www.jimpugel.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** (206) 286-0410
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
የተወለድኩት በሲያትል ውስጥ ሲሆን ሕይወቴ ሙሉ በሙሉ እዚህ ነው የኖርኩት። በመንግስት እና በግል ዘርፎች ውስጥ ካሉ የተለያዩ ህዝቦች ጋር አስርተ ዓመታትን በመጠበቅ እና በመስራት አሳልፌያለሁ። በማኅበረሰባችን ላይ ለተጋረጡ በርካታ ችግሮች እውነተኛ ለውጥን ለማምጣት ለከተማው ምክር ቤት [City Council] እወዳደራለሁ። እንደ አቅምን ያገናዘቡ፣ አካታችነት፣ መጓጓዣ እና ተንቀሳቃሽነት የመሳሰሉ ጉዳዮች። የእኔን ተጨባጭ ሙያ በህዝባዊ ደህንነት፣ የሰብአዊ አገልግሎቶች እና የእኛን መብቶች ጥበቃ እና ተራማጅ እሴቶችን ወደ ምክር ቤቱ አመጣለሁ። ሲያትል የተገነባችው ከየትኛውም የኑሮ ደረጃ ባሉ ሰዎች ደጋፊ በሆኑ በታላቅ የሰፈር አካባቢዎች ነው። በአብዛኛው ጎረቤቶቻችንን ለችግር የሚዳርግ የተመጣጣኝነት ቀውስ ሲገጥመን፣ ህዝባዊ እምነትን በሚገነባ መንገድ፣ ግልጽነትን እና በሲያትል ውስጥ ለሁሉም ሰው እንደ መኖራችን ያለንን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ መልኩ ማደጋችንን ማረጋገጥ አለብን። ድምጽዎን ባገኝ ክብር ይሰማኛል።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** Michael George
**የዘመቻ ስም፡-** ሰዎች ለ Michael George
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** http://www.michaelforseattle.com
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** (206) 513-3664
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**

Michael George ተጠያቂነት እና ተጨባጭ አስተሳሰብን ወደ ከተማው አስተዳደር ለማምጣት እየተወዳደረ ነው። እሱ ለሁሉም እድሜዎች እና ገቢዎች የመኖሪያ ቤት ተደራሽነትን ለመጨመር፣ ሰዎች በከተማዋ በኩል እንዲያገኙ ቀለል ማድረግ፣ መጠለያ የሌላቸውን ጎረቤቶቻችን የደረሰባቸውን ቀውስ መፍታት እና ሲያትልን ለረዥም ጊዜ ስኬት ለማዋቀር ቁርጠኛ ነው። በበርካታ የሲያትል ውስብስብ የመኖሪያ ቤት እና የመጓጓዣ ውጥኖች ውስጥ በመስራት Michael ተጨባጭ የእውነተኛ-ዓለም ተሞክሮን ወደ ምክር ቤት ያመጣል እና አካታችነት እና መንደር ለኑሮ አመችነት የማመጣጠን ተግዳሮቶችን ይረዳል።

Michael ከባለቤቱ እና ከሁለት ወጣት ልጆቹ ጋር መሃል ከተማ ይኖራል። Michael ወላጆች ለተሻለች Seattle መሃል ከተማ (Parents for a Better Downtown Seattle) ፣ መሃል ከተማ ለልጆች የተሻለ የመኖሪያ መንደር ለማድረግ ያለመ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት በጋራ-ይመራል። Michael የህዝብ ት/ቤቶች የአቅም ግብረ ሃይል ሆኖ አገልግሏል፣ ሲያትል ለሁሉም የእድሜ ክልሎች እና የገቢ አይነቶች ሆና እንድታገለግል ያለሙ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ውጥኖች ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ሰርቷል።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ እየተሳተፉ ነው።*

**የእጩው ስም፡-** ናቬድ ጃማሊ [Naveed Jamali]
**የዘመቻ ስም፡-** ናቬድ ለ ሲያትል [Naveed for Seattle]
**የዘመቻ ድረ-ገጽ፡-** http://naveedforseattle.com/
**የከተማ አስተዳደር ዲስትሪክት ቁጥር፡-** 7
**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** (425) 954-3286
**የእጩ ማስተዋወቂያ፡-**
ሲያትል የመሪነት ከፍተኛ ችግር አለባት። የእኛ የከተማ ምክር ቤት [City Council] በተጨባጭ ችግሮች ላይ ተጨባጭ መሻሻሎችን ማምጣት አልቻለም።
የእነርሱን የወደቀ፣ ከፋፋይ የሆኑ ፖሊሲዎችን ለመጣል እና ሁሉንም መራጭ ህዝብ በመወከል በጥንቃቄ እና በትኩረት ሊሰሩ የሚችሉ ተወካዮችን ለመምረጥ እድላችን ይሄ ነው። ለ ዲስትክት 7 [District 7]፣ ናቬድ ጃማሊ [Naveed Jamali] ግልጽ ምርጫ ነው።
ናቬድ [Naveed] ህይዎቱን የህዝብ ደህንነትን ለማስጠብቅ ሰጥቷል። እውነተኛ መሪነት እውነትን ፈንቅሎ ለማውጣት ተነሳሽነት፣ ስህተትን የመቀበል ትህትና፣ እና ለወደፊት የሚያስኬዱ አዳዲስ መንገዶችን ለመሞከር ድፍረት እንደሚያስፈልገው ያውቃል። ለበለጠ ታላቅ ነገር መስዋትነትን መክፈል ማለት ምን እንደሆነ ያውቃል።

ናቬድ [Naveed] የአሜሪካ ባህር ሃይል [US Navy] የደህንነት መኮንን፣ ደራሲ፣ እና የቀድሞ MSNBC ተንታኝ ነው። በቢሮ ውስጥ ስላደረገው የሲቪል ስራዎች ከ ኤፍቢአይ ዳይሬክተር ሮበርት ሙለር [FBI Director Robert Mueller] የምስጋና ምስክርነቶችን አግኝቷል። በሳንዲ ጦሮ አውሎ ንፋስ [Hurricane Sandy] ከስተት በኋላ ላደረገው አገልግሎት የኒው ዮርክ የሰብዓዊነት ሜዲያል [ New York's Humanitarian Medal] ተሸልሟል። ከሚስቱ እና ከልጆቹ ጋር በኩን አን [Queen Anne] ውስጥ ይኖራል።

*እኚህ እጩ በዲሞክራሲ ቮውቸር መርሀግብር (Democracy Voucher Program) ላይ አይሳተፉም።*